# ወደ ክርስቶስ የሚያድግ ጤናማ ሕይወት (ክፍል 2)

## 4. ይቅርታ የሚጠይቅና እርሱም ሌሎችን ይቅር ማለት የሚችል

- ይቅርታ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ፈጽሞ መዘንጋት የሌለበት ተግባር ነው

- የቅርታን በሕይወቱ የማይለማመድ አማኝ ክርስትናው አጠያያቂ ነው።ይህ እንቢተኝነት ቀይቶ መንፈሳዊ ጉዳት ሊያስከትል የችላል *ለምሳሌ ፦* አቤሴሎም 2ነገ 13
- ስንት ጊዜ ይቅር ልበል? (ማቴ18፣21-23)
  - ክርስቶስ በምድር ሳለ ስለ ይቅርታ በተደጋጋሚ ያስተማራቸው ትምህርቶች በጣም በርካቶች ናቸው (ሉቃ15፣11-32 ; ማቴ18፣25-35)

- አማኞች ይቅር ማለት ያለብን ለምንድነው ?
  - እ/ርን በየትኛውም መልኩ ስንበድለው ይቅር ስለሚለን ማቴ 6፣12-15

- በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ካልሆነ በስተቀር ይቅርታ መጠየቅም ሆነ መስጠት የማይቻል ነገር ነው (ሐዋ7፣59-60)
  - ምክንያቱም - የተበደልነው በደል ሁልጊዜ ስለሚገዝፍብን
    - የበደለንን ሰው ሆነ ብሎ የደረገው ስለሚመስለን
    - በኅብረተሰባችን ውስጥ የቅርታን ተለማምደነው ባህል ባለመሆኑ

- ይቅርታ የሚያስጠይቅ ነገር እያለ የሚመለከተው ሰው ወይም ቡድን ከማድረግ ቢቆጠብ እ/ር ያንን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ ስለ ሚወስድ እኛ ግን ከልባችን ይቅር ማለትን አንተው (1ሳሙ25)
  - በንስሀ ልብ ካልተመለሱ እ/ር ይበቀላል (1ጴጥ4.19፤ ሮሜ12፣17-19)

- በትክክል ይቅርታ ማድረጋችን የሚታወቀው
  - ይቅር የልነውን ነገር በምንም መልኩ የማናነሳው ከሆነ
  - በዳያችን በገጠመን ቁጥር ልባችን በጥላቻ፣ በንዴት፣በንቀትና ባለመቀበል የማይሞላ ሲሆን
  - ለበዳያችን ስንጸልይለት፣መልካም እንዲሆንለት ስንመኝለት፣ስንባርከው እና በጎ ነገርን ስናደርግለት

## 5. እ/ርን በነገር ሁሉ የሚያመሰግን ሕይወት

- እ/ር ሰውን ከፈጠረበት ዋነኛ አላማዎቹ መካከል እርሱን እንዲያ

መሰግኑት ነው
- አለማመስገን የተፈጠርንበትን ዓላማ መሳት ነው
- የማያመሰግኑ በመጨሻው ዘመን ይበዛሉ (2ጢሞ3፣2)

- የምናመሰግንበት አስደናቂና ብዙ የእ/ር ስጦታዎች አሉ
  - በሕይወትህ የምታመሰግንበት ምን ነገር አለህ/ሽ ? (መዝ139፣14)

- የእ/ር ስጦታዎች <u>ድንቅ</u> መሆን እ/ር ለእኛ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ያመለክታሉ (ዮሐ15፣13)
  - ስጦታዎቹ ተራና በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም (ምሳሌ ፦ ደህንነታችን)

- የእ/ር ድንቅ ስጦታዎች ሁሉ እኛ ስለተገባን ሳይሆን እንዲሁ በእርሱ ቸርነት የተሰጡን ናቸው (ዘዳ7፣6-8)

- የተሰጡንን ክቡር ስጦታዎች ለማይገባን ለእኛ ስለተሰጡ ከእውነተኛ ልብ የሚፈልቅ ሙሉ ምስጋና እንድናቀርብ ያነሳሱናል

- ምስጋናችን በልዩ ልዩ መልክ ሊገለጽ ይችላል
  <u>ለምሳሌ</u> ፦ በቃል፣ በዜማ፣ በተግባር፣ በኑሮ፣ በአምልኮ

## 6. <u>በቅንነትና በትህትና የተሞላ ሕይወት</u>

- በሕይወቱ <u>ቅን</u> የሆነ ሰው ፦ ለምሳሌ ፦ ኢዮብ፣ዳንኤል ...
  - ለሌላው ሰው የሚጠቅመውን ነገር ይመለከታል
  - ለሌሎች እድልን የመስጠት አመለካከት አለው
  - ሌሎች የሚያደርጉትን ሆነ የሚናገሩትን ቃል በቀና መልኩ ብቻ ይረዳል ሆኖም ክፉውን ነገር በመንፈስ የመዝናል
    - ጠማማ አይደለም (መዝ 25፣8)
- በሕይወቱ ትሁት የሆነ አማኝ ከእ/ር ጸጋ በስተቀር የሚኩራራበት ነገር የለውም (1ቆሮ15፣10)
  <u>ምሳሌ</u> ፦ ሐዋ/ጳውሎስ
  - ...ከኃጢያተኞችም ዋና በምሆን... 1ጠሞ15-16
  - ...እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ... 1ቆሮ15፣8
  - ...ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ... ኤፌ3፣9

- ትሁት ሰው ያለው ነገር ሁሉ ከእ/ር ፍቅርና ምህረት የተነሳ መሆኑን በጽናት ይረዳል
  - መንፈሳዊ ይሁን ምድራዊ በረከት፣ ያለው ልዩ ተሰጥዎም ይሁን ችሎታ
    <u>ምሳሌ</u> ፦ ንጉሥ ዳዊት እና ንጉሥ ኦዝያን

® ስኬትን ስናገኝ ልባችን ትሁት መሆኑን ወይም አለመሆኑን እናረጋግጥ

- ትሁት ሰው ስላለው መልካም ነገር ሁሉ ክብሩን ለእ/ር ይሰጣል (ሮሜ15፣18-19)

- በስሜት ራሱን ደሃና ምስኪን ኃጥያተኛ አድርጎ የተናገረ ሁሉ ትሁት አይደለም

7. *<u>በእ/ርና በሰው ሁሉ ፊት በንጹህ ልብና ሕሊና የሚመላለስ</u>*
   - *መዝ* 51፣10 ...*አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ*
   - *ሐዋ* 24፣16

- ከእ/ር ጋር የላስተካከልነው ነገር ሲኖር በንጹህ ልብ በእርሱ ፊት መመላለስ ያዳግተናል (*መዝ* 15)
  - እ/ርን በድለን ሊሆን ይችላል
    *መፍትሄው ፦ ንስሀ መግባት*
  - እ/ር እየተናገረን ያለውን ነገር ባለማድረጋችን ሊሆን ይችላል
    *መፍትሄው ፦ እርሱ የሚለንን መስማት*

- አንዳንድ ጊዜ *<u>ከምንሰማው ነገር</u>* ብቻ ተነስተን በሰዎች ላይ በጎ ሕሊና ልናጣ እንችላለን
  - *...ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ*

- አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰለ ሌሎች ሰዎች *<u>የምንገምታቸው ነገሮች</u>* ይኖሩንና በዚያ አእምሮአችን ሊያዝ ይችላል

- ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚያገናኘን ነገር ላይ የተለያየ አቋም ይኖረንና ያለን ግንኙነታችን እየሻከረ ከሄደ
  - *መፍትሄው ፦ ግንኙነታችንን ማስተካከል*